# ኪንግ ካውንቲ የአካባቢ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣን ትዕዛዝ - የክትባት ማረጋገጫ

በዴልታ ዝርያ ምክንያት በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የ COVID-19 ክስተቶች እና  ሆስፒታል የሚተኙት እንዲሁም የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። እነዚህን ክስተቶች እና ሞትን በክትባት መከላከል ይቻላል። ስለዚህ ፣ የህዝብ ጤና-የሲያትል እና የኪንግ ካውንቲ የጤና ኦፊሰር ዶክተር ጄፍ ደቺን ለተወሰኑ የቤት ውስጥ እና የውጭ ዝግጅት ማቅረቢያ ቦታዎች እና ተቋማት ደንበኞቻቸውን ሙሉ ክትባት መውሰዳቸውን ማረጋገጫ  ወይም አሉታዊ የ COVID-19 ምርመራ እንዲያሳዩ እንዲጠይቁ የአከባቢ ጤና መኮንን ትዕዛዝ ሰጥቷል። ክትባት COVID-19 ን  ለመከላለል የእኛ ተመራጩ መሣሪያ ነው።

### አዲሱ ፖሊሲ የሚከተሉትን ነገሮች ያጠቃልላል:

ከኦክቶበር 25 ፣ 2021 ጀምሮ ደንበኞች እነዚህ ቦታ ውስጥ ለመግባት በኤፍዲኤ (FDA) ወይም በዓለም የጤና ድርጅት (WHO) የፀደቀ የ COVID-19 ክትባት ማረጋገጫ ማሳየት አለባቸው፡

- **የውጭ ዝግጅት ቦታ ላይ** ከ 500 ወይም ከዛ በላይ ሰዎች በሚገኙበት የውጪ ዝግጅት ቦታ ላይ (እንደ ሙያዊ እና የኮሌጅ ስፖርት መስጫ ቦታዎች እና የመዝናኛ ቦታዎች)
- **የቤት ውስጥ የመዝናኛ ዝግጅት ቦታዎች ወይም ተቋማት ላይ**፣ ህዝብ የመያዝ አቅማቸው ምንም ይሁን ምን (እንደ ሙያዊ እና የኮሌጅ ስፖርቶች ፣ የስነጥበብ ሥራ ቦታዎች እና ሙዚቃ ሥፍራዎች ፣ የፊልም ቲያትር ቤቶች ፣  ጂሞች እና የኮንፈረንስ/የስብሰባ መስጫ ቦታዎች)
- **ምግብ ቤቶች እና ቡና ቤቶች ላይ** ይህ የቤት ውስጥ መመገቢያ ቦታዎችን ይመለከታል። ስለዚህም ከቤት ውጭ ያሉ የመመገቢያ ቦታዎችን ፣ ቴክአውት ደንበኞችን እና በዋናነት እንደ ምግብ ቤት የማያገለግሉ ቦታዎችን ለምሳሌ እንደ የምግብ መደብሮችን አይመለከትም። ትዕዛዙ 12 ወይም ከዚያ በታች የመቀመጫ አቅም ላላቸው አነስተኛ ምግብ ቤቶች እና ቡና ቤቶች ረዘም ያለ የዝግጅት ጊዜ አማራጭን ይሰጣል ፣ ከዲሴምበር 6 ቀን ጀምሮ።

ተቀባይነት ያለው የክትባት ማስረጃ ሰነድ ምንድን ነው?

- የሲዲሲ (CDC) COVID-19 ክትባት ካርድ ወይም የክትባት ካርድ ፎቶ
- የታተመ የምስክር ወረቀት ወይም የ QR ኮድ (መስከረም መጨረሻ ላይ) በ MyIRMobile.com ድህረ-ገፅ ውስጥ ይገኛል  (ድህረ-ገፁ በእንግሊዝኛ ብቻ ነው)
- ከዩናይትድ ስቴትስ ወይም ከሌላ ሀገር የተሰጠ ሌላ የመንግስት የክትባት መዝገብ ፣ የህክምና አገልጋዮችንም ጨምሮ። የመዝገቡ ካርድ ፎቶ ወይም ፎቶ ኮፒውም ሊሆን ይችላል።

**ማሳሰቢያ** - ከሀኪም ወይም ከሀይማኖት ተቋማት ክትባት እንዳይወስዱ የሚፈቅድ መረጃ ተቀባይነት የለውም። ከክትባት ማረጋገጫ ሰነድ ጋር የመታወቂያ ካርድ ማሳየት አያስፈልግዎትም።

ላልተከተቡ ወይም የክትባት ሁኔታቸውን ማረጋገጥ ለማይችሉ ሰዎች የተሰጡ አማራጮች

ክትባት ያልተከተቡ ወይም የክትባት ሁኔታቸውን ማረጋገጥ የማይችሉ ሰዎች የሚከተሉትን ማስረጃ ማሳየት አለባቸው፡

- ባለፉት 72 ሰዓታት ውስጥ የተወሰደ የ ፒሲአር (PCR) COVID-19 አሉታዊ ምርመራ ማረጋገጫ ፣ ወይም በቶሎ መልስ ከሚሰጡ የምርመራ ጣቢያዎች የተሰጠ የፈጣን አሉታዊ ምርመራ ውጤት ማሳየት አለብዎት። ተቋማቱ የክትባት ማስረጃን ወይም አሉታዊ የምርመራ ሁኔታን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ትዕዛዙን ለሚተገብሩ ንግዶች እና ድርጅቶች የቴክኒካል ድጋፍ እና ትምህርታዊ ቁሳቁሶችን ለማቅረብ የህዝብ ጤና ተቋም አብሮ ይሠራል።

## የፖሊሲ ልማት

ኪንግ ካውንቲ እና የህዝብ ጤና ተቋም ይህንን ፖሊሲ ያወጡት በመላው ካውንቲ ውስጥ ከሚገኙት ከህዝብ ጤና ወረርሽኝ እና ዘረኝነት ማህበረሰብ አማካሪ ቡድን ፣ ከከተሞች ፣ ከአነስተኛ ንግዶች ፣ ከንግድ ምክር ቤቶች ፣ ከሠራተኛ ማህበራት ፣ ከንግድ ማህበራት ፣ ከስፖርት ቡድኖች ፣ ከዝግጅት ቦታዎች ፣ ከማህበረሰብ ቡድኖች ፣ በእምነት ላይ ከተመሠረቱ መሪዎች ጋር በመመካከር ነው። አላማቸው ለንግድ እና ለነዋሪዎች የሚሰራ ፣ ፍትሃዊ እድል ለመፍጠር ነው።

**ለበለጠ መረጃ [kingcounty.gov/verify](kingcounty.gov/verify)ይመልከቱ (የተተረጎሙ የመረጃ አቅርቦቶች ይገኛሉ)**